
# <u>ኢ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2019 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት የተጠናከሩበት ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ በተለይም ከአስሩ ቀናት አጋማሽ ጀምሮ ወደ ሀገራችን ይገባ የነበረዉ እርጥበት አዘል አየር የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበረዉ፡፡ በዚህ መሰረት በምስራቅ ትግራይ እና አማራ፣ በመካከለኛዉ፣ በምዕራብ እና በደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጥቂት የደቡብ አፋር እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በቡሬ 43.3፣ በጊኒር 36.5፣ በአይራ 35.5 እና በአርጆ 31.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከፊል ደመናማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከትግራይ ክልል በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደርና በምስራቅ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ክልል በምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጅማ፣ በምሰራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌና አርሲ፣ በጉጂ እና በቦረና ዞኖች፤ ከሞላ ጎደል በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ዞኖች እንዲሁም በጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ ከ 5-112 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በደቡብ ትግራይ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በኢሉአባቦራ እና ምስራቅ ወለጋ፣ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የሸካ፣ ቤንች ማጂ እና ደቡብ ኦሞ እንዲሁም ጥቂት የባሌ ዞን አካባቢዎች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ወቅት የተሻለ ዝናብ ማግኘት የነበረባቸው የሀድያና ጉራጌ፣ የአርሲና የባሌ ዝቅተኛ ስፍራዎች፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ የደቡብ ኦሮሚያ አብዛኛው ቦታዎች፣ እንዲሁም ምስራቅና ምዕራብ ሸዋ ዞኖችን ጨምሮ የዝናብ እጥረት የተፈጠረባቸው ሲሆን፤ <u>ይህም ሁኔታ በሞዛምቢክ ቻናል ላይ በተፈጠረው ያልተጠበቀ የአጭር ጊዜ ዝቅተኛ የአየር ግፊት (ሳይክሎን) ምክኒያት ወደ ሀገራችን ይገባ የነበረውን እርጥበት አዘል አየር እንዲቀንስ አስተዋፅዖ ያደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከላይ በተቀስናቸው ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡</u> በቀሪዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይም ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ።


ካርታ1    ኢ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ ማርች 31/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2 ኢ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ ማርች 31/2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ3   እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ ማርች 31/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከማርች 21- 31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው  ተጽዕኖ

ባሳለፍናቸው የማርች የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በአንፃራዊነት መሻሻል የታየበት እንደነበርና በተለይም የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች እርጥበታማ ገፅታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለሚዘሩ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት አስቀድመው የማሳ ዝግጅት እንዲያከናውኑና በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥሩ አጋጣሚ ነበረዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት በአካባቢዎቹ ለሚኖሩት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ባሳለፉት ቀናት የተከሰተውን የእርጥበት እጥረት እንድሻሻል ከማድረግ አንጻር  ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረዉ (ካርታ 4) ፡፡


**ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረዉ የዕርጥበት ሁኔታ**



# <u>እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 21-31 ማርች 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው የላይኛውና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና ደቡባዊ አባይ፣ በጥቂት የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ተከዜ፣ የታችኛዉ ስምጥሸለቆ እና በአብዛኛው ኦሞጊቤ አዋሳኝ ከፍተኛ ኪስ ቦታዎች ናቸው። በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ በጥቂት የደቡባዊና ምስራቃዊ አባይ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ባሮአኮቦ፣ የደቡባዊና ታችኛው ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ እና የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ናቸው። የተቀሩት አብዛኛው ተከዜ፣ አዋሽ፣ የአባይ ምእራባዊ አጋማሽ፣ ኦጋዴን፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እና ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5) ።

**ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረዉ የዕርጥበት ሁኔታ**



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2019 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት ከቀዳሚው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በበልግ ዝናብ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ አዲስ አበባ፤ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፤ አርሲና ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ ሁሉም የጋምቤላ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ ጥቂት የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5 ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ፣ እንዲሁም የሰገን ህዝቦች በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የአፕሪል ወር የመጀመሪያው አሥር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በበልግ አብቃይ አካባቢዎች የሚሻሻልበትና የበልግ ሰብሎችን፣ ቋሚ ሰብሎችን እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚቻልበት ወቅት ሲሆን፣ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥለዉ የአፕሪል ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በመጠንም ይሁን በስርጭት በተለይም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እንደሚሆን በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም ሁኔታ በትንበያው ላይ ለተጠቀሱት የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፣ በተለይም ባሳለፍናቸው አስር ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች በነበሩት ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት ጋር

ተያይዞ የተፈጠረውን የእርጥበት እጥረት እንደሚያረግብ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚኖረዉ የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሮች ዝግጅት ሊያደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን ውኃ ማጠራቀምና በመሀል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኤፕሪል 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የዝናቡ ስርጭትና መጠን በተሻለ መልኩ እንደሚስተዋል ትንቢያው ይጠቁማል። በመሆኑም በመጪዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ አባይ፤ የላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ፣ ተ□ዞ⊡ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ እና ገናሌዳዋ እንዲሁም የታችኛዉ አዋሸ ተፋሰሶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በበልግ ወቅት ከፍተኛ ሙቀት ስለሚኖር በትነት ምክንያት ብዙ ውሃ እንዲባክን አስተዋፆ ያደርጋል። በሌላ በኩል የበልግ ዝናብ መኖር የውሃ እጥረትን ለማካካስ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ በተፋሰሶች ላይ የሚገኘውን ዝናብ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የዝናብ ውሃ መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን።